የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08135 ሐምሌ 7 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ብይን በተጠሪና በሥር ተከሣሽ መሃከል እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ሁኔታ አለ እንዲሁም የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ቤት በዚህ ግንኙት መሃል የተፈራ ነው በማለት የሰጠው ትችት ውድቅ ተደርጓል፡፡ የእግድ ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም ሲል የሰጠውን ብይን ግን ፀንቷል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 51866

ሐምሌ 02 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፣** ወ/ሮ ደጅይጥኑ አለማየሁ - ቀረቡ

**ተጠሪ፣** ወ/ሮ አዛለች ደበብ - ጠበቃ ደርበው ተመስገን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የጋብቻ ማስረጃን መስጠት በመቃወም የተጀመረ ነው፡፡ የጉዳዩ አጀማመር ለተጠሪ የተሰጠ የጋብቻ ማስረጃ አለአግባብ ነው፤ ሊሰረዝ ይገባል በማለት አመልካች መቃወሚያ በማቅረባቸው የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቀደም ሲል ለተጠሪ የሰጠው ማስረጃ በመሰረዝ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ በተጠሪ እና በሟች መካከል ጋብቻ መኖሩን አምነው ጋብቻው ፈርሷል የሚል መከራከሪያ ያቀረቡ ስለሆነ ጋብቻው ፈርሷል? አልፈረሰም? የሚለውን ማጣራት ይገባው ነበር ካለ በኃላ በዚህ ምክንያት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት በዚሁ ላይ ሲሆን ይዘቱም በተጠሪ እና በሟች ጫኔ በዛብህ መካከል ጋብቻ አልነበረም አለ ከተባለም በሕይወት እያሉ ተፋትተው የተለያዩ በመሆኑ ይህ ሳይጣራ የተሰጠው ውሣኔ አለአግባብ ነው ሲሉ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጋብቻ ፈርሷል ወይስ አልፈረሰም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ በራሱ ሳያጣራ ወይም በሥር ፍ/ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን ሳያደርግ በደፈናው የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል የተጠሪ ጠበቃ ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ መልስ

አቅርበዋል በይዘቱም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ እንዲፀና ያመለከቱበት ነው፡፡

እኛም የክርክሩን አመጣጥ አስመልክቶ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመረ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ከሥር መዝገብ መረዳት የተቻለው አመልካች ለተጠሪ የተሰጠው የጋብቻ ማስረጃ እንዲሰረዝ አቤቱታ ሲያቀርቡ በተጠሪ እና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ ቀድሞ ፈርሷል በሚል መነሻ ምክንያት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በሟች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ነበር ወይስ አልነበረም? ጋብቻ ነበር ከተባለ ቀድሞ በፍቺ የፈረሰ ወይንስ በሟች ሞት ምክንያት? የሚሉት ነጥቦች በአግባቡ ሳያጣራ የተወሰነ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም በውሣኔው በግልፅ እንዳመለከተው በተጠሪ እና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል? ወይስ አልፈረሰም? የሚለው ነጥብ ያልተጣራ መሆኑ ሲረዳ ይህ ነጥብ እንዲጣራ ማድረግ አሊያም ሥር ፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲጣራ ማድረግ ይገባው ነበር ይህ ሳይጣራ በደፈናው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር ብቻ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት አግኝቷል ለማለት አያስችልም ምክንያቱም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ በግልፅ በመቀበል ወይም ባለመቀበል የተሰጠ ውሣኔ ባለመኖሩ ነው፡፡ ስለሆነም የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሙግት አመራር እና ጭብጥ አያያዝ ስህተት ያለው መሆኑን ከተረዳ ማረም ሲገባው ማለፉ እና የአመልካችን ጥያቄ ግልፅ ዳኝነት ያልሰጠበት ከመሆኑም አንፃር በክርክሩ አመራር ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶች ሰበር ችሎትም ይህንን ማረም ሲገባው ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡

ስለሆነም ይኸው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ በመ/ቁ 1234/99 በ3/01/02 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10849 በ9/03/02 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአ.አ ከተማ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በመ/ቁ 12433 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በሟች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ ነበር በአመልካች ስላልተካደ፤ ጋብቻ ነበር ከተባለስ ጋብቻው በፍቺ ፈርሷል? አልፈረሰም? የሚለው የአመልካች መቃወሚያ ነጥቦች ላይ ግራቀኙን አከራክሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መዝገቡን ለአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ እንዲመለስ አዝዘናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

ም.አ